# ፖሊሲ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

***ተዛማጅ ሠነዶች፡-*** ABA-RA, ABA-EA, ABC, ACA, BFA, BFA-RA, BMA, IOD, IOD-RA, KBA
***ሀላፊነት ያላቸው ቢሮዎች፡-*** *የሰራተኞች ሀላፊ ቢሮ፤ የስልታዊ ስራዎች ሀላፊ፤ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ሀላፊ*

## የማህበረሰብ ተሳትፎ

A. **ዓላማ**

በህፃናት/ልጆች ላይ ተፅዕኖ ያላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ውሳኔዎች ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰብን ተሳታፊ ለማድረግ አካታች፣ ምላሽ ሰጪ ባህል፣ እና ከዘረኝነት የፀዳ ተሳትፎ የሚከናወንበት መመሪያዎችን፣ መዋቅሮችን እና ተግባራዊ የሚደረጉ አሰራሮችን ማዳበር እና ማጎልበት ላይ የቦርዱን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ።

የሁሉም ተማሪዎች ፍትሀዊ የትምህርት ውጤቶች፣ ስኬት እና ደህንነት እንዲኖር የተማሪዎች፣ የወላጆች፣ የሰራተኞች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰብ ሌላ ፍላጎት ያላቸው አባላት ተሳትፎ አስፈላጊነት ላይ የቦርዱን ጠንካራ ዕምነት ለማረጋገጥ።

በተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች፣ ት/ቤቶች እና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ውስጥ ግንኙነትን ለማጠናከር በቦርድ ውሳኔ-አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ስለማህበረሰብ ተሳትፎ ደረጃዎች ጥናትን-መሰረት ያደረጉ መመሪያዎችን ለማዘጋጀት።

የማህበረሰብን ብዝሃነት እና ተሞክሮዎች የሚያንፀባርቁ የባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ አግባብነት ያለው እና ምላሽ ሰጪ ባህል ያለው አሰራሮችን እና መዋቅሮችን እንደሚፈልግ እውቅና ለመስጠት።

B. **ጉዳዩ**

1. የብዝሃነት ስብጥር ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሰራተኞች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ሀሳቦች፣ ፍላጎቶች፣ እንዲሳኩ የሚጠበቁ ነገሮች፣ እና ስጋቶችን መገንዘብ እና ዋጋ መስጠት ሁሉንም ተማሪዎች ለኮሌጅ፣ ለስራ እና ለማህበረሰብ አገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ የተቀመጠውን የዲስትሪክቱን ግብ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

2. ቦርዱ ውጤታማ፣ አካታች እና ፍትሀዊ ተሳትፎን የማዳበር አሰራሮችን ውስብስብነት፣ እና ለባለድርሻ አካላት እና ለሰራተኞች የአፈጻፀም መመሪያዎችን እና መዋቅሮችን አስፈላጊነት ይገነዘባል። ግልፅ የሆኑ የሚጠበቁ ነገሮች፣ መመሪያዎች እና ግብዓቶች አስፈላጊ ናቸው፣ የዚህም ምክንያት በአንዳንድ ውሳኔዎች ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ ወይም በተለምዶ አመለካከታቸው ቦታ ያልተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት ከተሳትፎ ጥረቶች እንዳይገለሉ ለማድረግ ነው።

3. ከታች የተጠቀሱት ሂደቶች መመስረት ያለባቸው ጥናትን-መሰረት ባደረጉ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ጥምረት ሞዴሎች ላይ ነው፥ እና እነዚህም በግልፅ የተቀመጡ የህብረተሰብ ሚና አላማዎችን፣ ተገቢ ሪሶርሶችን ተደራሽ ማድረግ እና ትርጉም ያላቸው እና አካታች የጥምረት እና የህዝብ ተሳትፎ ተግባራትን/አክቲቪቲዎችን በሚዘጋጁበት ጊዜ፣ እና የተለያዩ አመለካከቶች የሚደመጡበት እና የጋራ መከባበር ባለበት አካባቢ ግምት ውስጥ የሚገቡትን ምላሽ ሰጪ ባህል ያላቸው ምህዳሮችን ለመፍጠር ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶችን ማከናወን ያስፈልጋል።

4. አንዳንድ የአሰራር ሂደቶች ተጨማሪ የተሳትፎ/ቅንጅት ፕሮቶኮሎች ሊያስፈልጓቸው ይችላሉ፣ እና የዚህ ፖሊሲ አላማ እነዚህን ሂደቶች መተካት አይደለም፣ በዚህ ብቻ ባይወሰንም የሚያካትቱት፥ ፖሊሲ FAA፣ የትምህርታዊ መገልገያዎች ዕቅድ፣ እና ደንብ FAA-RA፣ የትምህርታዊ መገልገያዎች ዕቅድ።

C. **ትርጉም**

1. የማህበረሰብ ተሳትፎ ግብ የማህበረሰብ አባላት አንድ ላይ እንዲመጡ የተደረገበት አላማ ነው። ለዚህ ፖሊሲ አላማዎች ሲባል፣ በሚከተለው መንገድ ግቦች በይፋ መገለፅ አለባቸው፡-

   a) ማሳወቅ ማለት ለህዝብ የተመጣጠነ እና ተጨባጭ መረጃን በመስጠት ችግርን፣ አማራጮችን፣ እድሎችን፣ እና/ወይም መፍትሄዎችን እንዲገነዘቡ መርዳት ነው፤ ወይም

   b) ማማከር ማለት ትንተናዎች፣ አማራጮች፣ እና/ወይም ውሳኔዎች ላይ ከህዝብ ግብረ-መልስ ማግኘት ነው፤ ወይም

   c) ማሳተፍ ማለት በአጠቃላይ ሂደት ውስጥ ከህዝብ ጋር በቀጥታ በመስራት የህዝብ ፍላጎቶችን እና የወደፊት ግቦችን በቋሚነት መገንዘብን እና ግምት ውስጥ ማስገባትን ማረጋገጥ ነው፤ ወይም

   d) መተባበር ማለት የተመከሩ መፍትሄዎችን ማዘጋጀት ላይ ለምክር እና ለፈጠራ ከህዝብ ጋር አጋርነት መፍጠር እና የሚያቀቧቸውን ምክረ ሀሳቦች በሚቻለው ከፍተኛ መጠን በውሳኔዎች ውስጥ ማካተት ማለት ነው።

2. የማህበረሰብ አባላት የሚወክለው ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች ትምህርት ከፍተኛ-ጥራት ያለው የህዝብ/ፐብሊክ ት/ቤት ስርዓት ላይ ትክክለኛ/ተገቢ ፍላጎት ያላቸውን አባላት ነው። እነዚህም የሚያካትቱት፣ እንደ ተገቢነቱ፣ MCPS ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሰራተኞችን እንዲሁም ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሰራተኞችን ወክለው የሚናገሩ/የሚያቀነቅኑትን፣ በዚህ ብቻ ባይገደብም የሚያካትተው፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎችን፤ ማህበረሰብን-መሰረት ያደረጉ ተቋማትን፤ ወይም ዘርን፣ ጎሳን፣ የቆዳ ቀለምን፣ ቅድመ አያቶችን፣ የስነ-ፆታ ምርጫዎችን፣ የቤተሰብ አወቃቀርን/የወላጅ የኑሮ ሁኔታን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ እድሜ፣ ብቃት (የእውቀት/ግንዛቤ፣ የማህበራዊ/የስሜት እና የአካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋ ወይም ሌላ የህግ ወይም በህገ መንግስት ጥበቃ የተደረገላቸውን መገለጫዎች ወይም ከሌሎች ጋር ግንኙነቶችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን የሚወክሉ ቡድኖችን፤ የንግድ፣ የሲቪክ፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን፤ የአካባቢ ቅድመ-መዋለ ህፃናት እና ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማትን፤ እና የአካባቢ፣ የስቴት እና የፌደራል ኤጀንሲዎችን ነው።

3. ተሳትፎ ማለት መተማመን ያለባቸው ግንኙነቶችን በተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ ወላጆች፣ ሰራተኞች፣ ት/ቤቶች፣ እና በቦርዱ መካከል፣ እና በቦርድ እና በሰፊው ማህበረሰብ መካከል የሚያጠናክሩ ተሞክሮዎችን መተግበር ነው።

D. **አቋም**

ቦርዱ የሚፈልገው ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ከፍተኛ-ጥራት ያለው ትምህርት የሚፈልጉ ባለድርሻ አካላትን አጠቃላይ ተሞክሮዎች፣ ፍላጎቶች እና እሴቶች የሚወክሉ የማህብረሰብ አባላትን ተሳትፎ ነው።

1. ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድልዎ የሌለበት፣ ፍትሀዊ፣ እና የባህል ብቃት ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ፣ ቦርዱ የሚያረጋግጠው በማንኛውም ፕሮግራም፣ ተግባር፣ ውሳኔ፣ ወይም እርምጃ ውስጥ፣ በተገለሉ የተማሪ ቡድኖች ላይ ስትራቴጂያዊ ትኩረት፣ በሁሉም ተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ መፍትሄ ለመስጠት ፍትሀዊ

ምልከታዎችን እና ምላሽ ሰጪ ባህል እና ከዘረኝነት ነጻ አካሄዶችን መተግበር አስፈላጊነት አለው።

2. ቦርዱ የውሳኔ-አሰጣጥ ሂደቶቹን ለማሳወቅ እና በቦርድ ፖሊሲዎች ማጎልበት፣ ይሄም በቦርድ ፖሊሲ BFA፣ ፖሊሲ ማውጣት ላይ በተቀመጠው መሰረት፣ እና በሌሎች ውሳኔዎች ላይ የማህበረሰብ ሃሳቦችን፣ አስተያየቶችን እና ምክረ ሀሳቦችን ለመስማት እና ግምት ውስጥ በማስገባት እድሎችን ለመስጠት ሊፈልግ ይችላል፣ ይሄም የተማሪዎችን የላቀ ፍላጎት እንደ መርህ በመጠቀም ነው። ምንም እንኳን ቦርዱ በማህበረሰብ ተሳትፎ ስትራቴጂ የተሰበሰበ የማህበረሰብ ግብዓትን በጥንቃቄ ግምት ውስጥ የሚያስገባ ቢሆንም፣ ቦርድ በኃላፊነት እንዲያከናውን-የተደነገጉ ስራዎች የመጨረሻው ሀላፊነት የሚያርፈው በቦርዱ ላይ ነው።

   a) ይሄ ፖሊሲ ተጣጥሞ የሚሰራው ከቦርድ ፖሊሲ ABC፣ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ፣ ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድልዎ የሌለበት፣ ፍትሀዊ፣ እና የባህል ብቃት፣ እና ቦርድ ፖሊሲ KBA፣ ለህዝብ መረጃ የማጋራት ፖሊሲ ነው፣ ይሄም የህዝብ/ፐብሊክ መረጃ ለሰፊው ማህበረሰብ በሚቻለው መጠን ተደራሽነትን ያዳብራል፣ እና የማስተርጎም እና በጽሑፍ የመተርጎም አገልግሎቶችን ይሰጣል።

   b) አብዛኛዎቹ የቦርድ ውሳኔዎች በቀጥታ ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ ስለሚፈጥሩ፣ በዚህ ፖሊሲ ላይ በተቀመጠው መሠረት የህዝብ ተሳትፎ ተግባራት ማካተት ያለባቸው በተቻለ መጠን ብዝሀነትን የሚወክሉ የተማሪ ቡድኖችን ነው።

3. ቦርዱ በማህበረሰብ-ተነሳሽነት የሚደረግ ተሳትፎን የውሳኔ-አሰጣጥ ሂደቶቹን ለማሳወቅ እና ማህበረሰቡ የወደፊት ግቦቹን፣ ስጋቶቹን እና MCPS የሚያጋጥሙትን ጉዳዮች ትንታኔዎች በሚመለከት በርካታ የማህበረሰብ ተሳትፎ እድሎችን ይሰጣል።

4. ቦርዱ፣ ዋናው ጽ/ቤት፣ እና የትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ምላሽ ሰጪ ባህል ያለው የተሳትፎ ዕቅድ እና የትግበራ መመሪያዎችን እና ግብዓቶችን በሁሉም የማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ በመነሻ ዕቅድ፣ በትግበራ እና ምዘናዎች ውስጥ መጠቀማቸውን ማስረጃ ያቀርባሉ። የተሳትፎ ግቦች (ለምሳሌ፡- ለማሳወቅ፣ ለማሳተፍ፣ ለማማከር ወይም ለመተባበር) በግልፅ መቀመጥ እና ለስራው ተገቢ መሆን አለባቸው፣ የተሳትፎ አስፈጻሚዎች የተሳትፎ ተግባራትን በሚነድፉበት ጊዜ ከዚህ በታች የተቀመጡትን የመመሪያ ጥያቄዎች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡-

   a) ተሳታፊዎች (ይህ ይበልጥ የሚነካው ማንን ነው? ውጤታማ የሆነ ውሳኔ ለማድረግ ማን ነው መሳተፍ ያለበት?)

   b) ተማሪዎች (የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብዝሀነትን በሚያንፀባርቅ መንገድ ተማሪዎች ተደማጭነት እንዲሰማቸው ለማድረግ መካተት የሚችሉት እንዴት ነው?)

   c) ተደራሽነት (ተሳታፊዎችን የማሳተፊያ ምርጥ ስልቶች ምንድን ናቸው?)

   d) ሂደት (የተሳትፎ ሂደቱ ተሳታፊዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ በምን መንገድ ነው የሚደራጀው እና የሚመቻቸው?)

   e) ምዘና (ጥረቶቻችን ውጤታማ እንደነበሩ የምናውቀው እንዴት ነው?)

5. ቦርዱ፣ ዋና ጽ/ቤት፣ እና የትምህርት ቤቶች ሰራተኞች የሁሉንም ብዙሃን የማህበረሰብ ተሳትፎ የሚተገብሩት እና የሚመዝኑት በሚከተሉት የመመሪያ ጥያቄዎች መሠረት ነው፡-

a) ይሄ ስራ ወይም ውሳኔ ማንን ነው የሚያገለግለው ወይም የሚያገለው?

b) በውይይቱ የማን ድምፅ ይበልጥ ተቀባይነት አለው/የጎላ ተፅእኖ ያደርጋል? ወይስ የማን ድምፅ በውይይቱ ተሰሚነት አላገኘም?

c) በዚህ ውሳኔ ምክንያት ምን ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖዎች ወይም ያልታሰቡ ውጤቶች ሊከተሉ ይችላሉ?

d) ቀጣይነት ያለው የመረጃ አሰባሰብ እና የውጤቶቹ ነፀብራቅ ምን ደረጃዎች አሉት?

e) የተለያዩ አይነት ማንነቶች እና አመለካከቶች ተወክለዋል ወይ? እና ስለ ስራው/ስለ ውሳኔው ትግበራ ግብዓት ሰጥተዋል ወይ?

6. የተሳትፎ ስልቶች ማንኛውንም ለተሳትፎ ግቦች ተገቢ የሆኑ እንደሚከተሉት አይነት መንገዶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ በዚህ ብቻ ባይገደቡም፡-

a) የማህበረሰብ-ተነሳሽነት የተሳትፎ መንገዶች፣ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ የህዝብ ምስክርነት፣ ከቦርድ አባላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት፣ ወይም ለቦርድ አባላት ወይም ለ MCPS አስተዳደሪዎች የማህበረሰብ ተቋማትን ስብሰባዎች እንዲካፈሉ የመጋበዝ ጥሪዎችን ያካትታል።

b) ሰፊ የማህበረሰብ ተደራሽነት ዳሰሳ ጥናቶችን፣ የህዝብ አስተያየት መረጃ ግኝትን፣ የማህበረሰብ ዝግጅቶችን፣ የቤት-ለቤት ግንኙነትን፣ ወይም በከፍተኛ መጠን የማህበረሰብ ግብዓት መቀበያ እና መተንተኛ ሌላ መንገዶችን በመጠቀም ይሆናል።

c) በተመቻቹ የአነስተኛ-ቡድን ውይይቶች፣ በአካል በመገናኘት ወይም በቨርችዋል መድረክ የሚደረጉ የጋራ ምክክሮች፣ በዚህ ቦታም የማህበረሰብ አባላት የሚፈልጓቸውን ርዕሶች ማስተዋወቅ፣ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ ወይም በዝግጅት አቅራቢዎች የተሰናዱ ርእሶች ወይም ጥያቄዎች ላይ መወያየት የሚችሉበት ነው፣ የሚያካትተውም–

(1) ተሳታፊዎች በተመቻቹ የአነስተኛ-ቡድን ውይይቶች እንዲሳተፉ እድል የሚሰጥባቸው የህዝብ ስብሰባዎች፤

(2) የጥናት ክበቦች፣ በአስቸጋሪ ርዕሶች ላይ እንዲሳተፉ እና የጋራ ስምምነት እንዲደረግ የሚረዱ ስለጠናዎች ለአመራሮች እንዲሁም ለተሳታፊዎች የሚሰጥባቸው መድረኮች፤

(3) የተሳታፊዎች የትኩረት ቡድኖች፣ በተለምዶ የሚመረጠው በጥቂት የጋራ ፍላጎት ያላቸው ወይም ተሞክሮዎች ላይ መሰረት በማድረግ ነው፤ ወይም

(4) የስራ ግብረ-ሀይል ወይም የባለድርሻ አካላት ስብሰባዎች፣ በተለምዶ የሚዋቀረው ከተሳታፊዎች መካከል የሚመረጠውም ቴክኒካዊ ጉዳዮችን የመተንተን የቴክኒክ ብቃታቸው ላይ መሰረት በማድረግ ነው።

d) በማህበረሰብ መድረክ ላይ ተሳታፊዎች መረጃ የሚያገኙባቸው፣ ምስክርነት የሚሰጡባቸው ወይም ጥያቄዎችን የሚጠይቁባቸው፣ ወይም ለተመቻቸ የአነስተኛ-ቡድን ውይይቶች እድል የሚያገኙባቸው የውይይት ወይም የትልቅ-ቡድን ስብሰባዎች።

6. የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባራትን ለመንደፍ፣ ለማመቻቸት እና ለማካሄድ እንዲቻል ተገቢውን ጊዜ፣ የገንዘብ ድጋፍ፣ ሙያዊ ትምህርት፣ እና MCPS ሰራተኞችን ለማቅረብ ቦርዱ በቁርጠኝነት ይሰራል።

   ቦርዱ የማህበረሰብ ተሳትፎ የተጠየቀበት ውሳኔዎች ላይ እርምጃ ከመውሰድ አስቀድሞ፣ ቦርዱ እንዲወያይበት/እንዲያስብበት በሚቀርቡ ጉዳዮች ውስጥ የሚከተለው መረጃ መካተት አለበት፡-

   a) የተካሄዱ የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባራት ማጠቃለያ፣ ይሄም ማካተት ያለበት የተሳታፊዎች መግለጫ፣ የተሳትፎው ግቦች፣ የተሳትፎው ውጤቶች፣ እና የማህበረሰብ አባላትን ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋሉትን ስልቶች፤

   b) ተማሪዎች እንዴት እንደተሳተፉ የሚያሳይ ማጠቃለያ ወይም ተማሪዎች ያልተሳተፉበትን ምክንያት ማስረጃ፤ እና

   c) የጋራ ስምምነት ምክረ ሀሳቦች የተገኙም እንኳን ባይሆን፤ ተለይተው የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎች እና/ወይም አማራጮች ላይ ማጠቃለያ።

7. የአካባቢ ትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን ብቻ የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ የቦርድ ውሳኔዎችን በሚመለከት፣ የት/ቤቱን ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ሰራተኞች ምርጫዎቻቸውን ለማረጋገጥ እና ለማክበር ቦርዱ ሁሉንም ጥረት ያደርጋል።

   a) ቦርዱ እንደ ተቀዳሚ አስፈላጊ ነገር አድርጎ የሚያረጋግጠው በአካባቢ ት/ቤቶች በኩል ተሳትፎዎችን በማድረግ በራሳቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት ማድረግን ነው።

   b) የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ እና የቴክኒክ እገዛ በማድረግ የአካባቢ ት/ቤት አስተዳደሪዎች ጤናማ/ጠንካራ የተሳትፎ ግቦችን እና ተግባራትን እንዲነድፉ እና እንዲተገብሩ ከዚህ ፖሊሲ ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ የማድረግ ሀላፊነት አለበት።

## E. ተፈላጊ ውጤት

የሁሉንም ነዋሪ ማህበረሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚያንፀባርቅ ይሆናል። MCPS ጋር በአጋርነት፣ የሁሉንም ተማሪዎች ፍትሀዊ የትምህርት ስኬት እና ደህንነት ለመደገፍ በክህሎት፣ በእውቀት፣ በሀሳብ፣ በልምድ እና በጊዜ ከሚደረጉት የብዙሃን ማህበረሰብ አስተዋፆ ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት በቂ-ግንዛቤ ይሰጣቸዋል የቦርድ ውሳኔን የሚመሩ ጉዳዮችን፣ እድሎችን፣ አማራጮችን፣ እና ሊተገበሩ የሚችሉ መፍትሄዎችን ይገነዘባሉ፤ እና የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት የወደፊት ፍላጎቶቻቸው/ግቦች፣ ስጋቶቻቸው እና ትንተናዎቻቸው እንዲደመጡ በርካታ የተለያዩ እድሎች ይኖሯቸዋል።

## F. የትግበራ ስልቶች

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፡-

   a) ምላሽ ሰጪ ባህል ያለውን የማህበረሰብ ተሳትፎ ለመደገፍ፣ እና የትግበራ መመሪያዎችን እና/ወይም ግብዓቶችን ለማዘጋጀት እና ለማሻሻል ሀላፊነት ያለው የጥምረት ኮሚቴ መፍጠር እና ስራውን ማስቀጠል፣ እና

   b) ለማህበረሰብ ተሳትፎ አካታች የሆነ፣ ምላሽ ሰጪ ባህል ያለው እና ከዘረኝነት ነጻ የሆኑ ስልቶችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል በሁሉም ደረጃዎች ላይ ለሰራተኞች ስልጠና እና ድጋፍ መስጠት።

2. እንደአስፈላጊነቱ በስርዓተ ትምህርት ጉዳዮች ላይ፣ ስለ መገልገያዎች፣ የገንዘብ/የባጀት ድጋፍ የሚመለከቱ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ ከፖሊሲዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የቦርድ ውሳኔዎች ላይ፣ የማህበረሰብ ግብዓትን፣ ተሳትፎን፣ ምክክር ወይም ትብብርን ቦርዱ የሚፈልገው በባህል እና በቋንቋ ብዝሃነት ካለው መጠነ ሰፊ ማህበረሰባችን ነው።

3. ከዚህም ባሻገር፣ በምን መንገድ የማህበረሰብ ግብዓት ግምት ውስጥ እንደገባ እና/ወይም ከእነሱ ተሳትፎ የተገኙ ውሳኔዎች ጥቅም ላይ እንደዋሉ ለተሳታፊዎች ለማሳወቅ ቦርዱ ተገቢ ስልቶችን ይቀይሳል።

## G. *ግምገማ እና ሪፖርት ማድረግ*

ይህ ደንብ በቦርድ ከተገመገመ በኋላ ክለሳ ይደረጋል።

**የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 287-74፣ ሜይ 28, 1974፤ ማሻሻያ የተደረገበት በውሳኔ ቁጥር 268-76፣ ሜይ 11, 1976፤ ማሻሻያ የተደረገበት በውሳኔ ቁጥር 346-06፣ ጁላይ 18፣ 2006፤ ማሻሻያ የተደረገበት በውሳኔ ቁጥር 327-13፣ ጁን 13, 2013፤ ማሻሻያ የተደረገበት በውሳኔ ቁጥር 47-23፣ ፌብሩዋሪ 7, 2023።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-  U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org